## Union of Tigreans in North America (UTNA)
### ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNA67@verizon.net

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703

09/09/2008

# ለህግ ልዕልና መከበር ሁሉም ዘብ ይቁም!!

እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የትግራይ ተወላጆች ማህበር አባላት ሰሞኑን ኢትዮጵያ-ጠቀስ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮችና ድረ-ገፆች በሰፊው ሲናኝ የከረመውን የሪፖርተር ዋና አዘጋጅ መታሰርን የተመለከተው ዜና የተከታተልነው በፅሞና ነው፡፡

ክስተቱ ለመፈፀሙ የድርጊቱ ሰለባ የሆነው ኣካል የሰጠውን ተከታታይ የመረጃ ምገባ በሰፊው ኣጢነናል፡፡ይህ ክስተት ለጊዜው ይፋ ሆኖ የሚያወያይ ጉዳይ ሆኖ ቢገኝም በአንፃሩም ደረጃው ከፍ ወይም ዝቅ ይል እንደሆነ ነው እንጂ በየእርከኑ የሚንፀባረቁ የህዝብ ቅሬታዎችና የፍትህ መጓደሎች እንሚስተዋሉ እሙን ሆኖ በክንዋኔው ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ ይኖር ዘንድ የሚመለከታቸው ኣካላት ሁሉ በበኩላቸው ጉዳዩን በማስመልከት ተገቢውን መረጃ በመስጠት ህዝብ ትክክለኛውን ግንዛቤ ይጨብጥ ዘንድ የድርሻቸውን ወቅታዊ መግለጫ ሊሰጡበት ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ክስተቱ እንደመነሻ የሚያነጋግር ጉዳይ ሆኖ ብቅ ያለ ቢሆንም ቁም ነገሩ በስፋትና በምልኣት የህግ የበላይነት፣ የፍትህ መከበር፣ የሰብኣዊ መብት መረጋገጥና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ጉዳይ ሆኖ ይስተዋላል፡፡

በኢትዮጵያ ረዥም የፖለቲካ መድረክ ታሪክ ላይ እስከኣሁን ስልጣን ላይ ከተፈራረቁት መንግስታት ውስጥ ለህግ ልዕልና መረጋገጥ፣ ለሰብኣዊ መብት መከበር፣ ለዜጎች የተናጠልና የቡድን የማይገሰስና የማይበረዝ ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ተግባራዊነት በፅናት የታገለ፣ መራራ መስዋእትነትም የከፈለና የቆመ ሃይል አሁን ስልጣን ላይ ያለው የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ መንግስት ነው፡፡ አብነቱም ባገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝቡን ሃቀኛ ፍላጎት ያካተተና የህዝቡን ሁለገብ ተሳትፎ ያረጋገጠ ህገ - መንግስታዊ ስርዓት በፅኑ መሰረትና መደላድል ላይ በመታነፅ ሂደት ላይ መገኘቱን ያጤነዋል፡፡

በመሆኑም ሰሞኑን በተከሰተው ጉዳይ ላይ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንደ ድርጅትና መንግስትም ጉዳዩ በቀጥታ ስለሚመለከተው ብቻ ሳይሆን መስዋእትነት የተከፈለበትና የስርዓቱም መሰረት በሆነው የህግ ልዕልናና ሃሳብን በነፃነት የማስተጋባት መብት ጥያቄ ላይ ማንኛውም ሁኔታ በሚያንዣብብበት በእንዳሁኑ ዓይነት አጋጣሚ የጉዳዩን ትክክለኛ ገፅታ በማቅረብና አስፈላጊውን መረጃ በመመገብ የህዝብን የማወቅ መብት በምልኣት ለማክበር ወቅታዊ መግለጫ ሊሰጥበት ማንነቱ የግድ ይለዋል፡፡

*መልካም አስተዳደር፣ ፍትህና እኩልነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ረዥም መንገድ ምስቅልቅል ሁኔታዎች፣ ፈታኝ ክስተቶችና እልህ አስጨራሽ ጋሬጣዎች መታየታቸው የትግሉ ውስብስብነት የማመላከታቸውን ያህል ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ባካተተ ህዝባዊ የሃላፊነት መንፈስ በየደረጃው መፍትሄ እንዲያገኙ ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ እና ህዝቡንም ያለምንም ብዥታ የግንባታው ባለቤት እና ተዋናይ ሆኖ ግንባር ቀደም ሚናውን ይወጣ ዘንድ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ አግኝቶ የችግሩ አካል ሳይሆን የመፍትሄው አጋር ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የማድረጉ ኣቢይ ቁምነገር መታለፍ ያለበት ጉዳይ አይደለም፡፡*

*የሚወሰደውም አቋም የዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ አካል ሆኖ ይቀጥልና ይዘወተርም ዘንድ መንግስት ሃላፊነቱን በሚገባ በመወጣት ወትሮም የቆመለትን ስርዓት በአስተማማኝ የማእዝን ድንጋይ መለሰኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የትግራይ ተወላጆች ማህበር አባላት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንደ ድርጅትና እንደ መንግስትም ጉዳዩ በቀጥታ እንደሚመለከተው አካል ጉዳዩን ኣስመልክቶ ህዝቡ የተሟላ ስዕል ይኖረው ዘንድና እንዲሁም የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምሰሶ የሆኑትን የግልፅነት፣ የሃላፊነትና የተጠያቂነት አሰራሮችን በሚያንፀባርቅ ሁናቴ ሁሉን ዳሰስ ማብራርያ በመስጠት ዜጎች ለህግ ልዕልና መረጋገጥ ዘብ በመቆም የድርሻቸውን በብቃት እንዲወጡ በተሸከመው የህዝብ አደራ መሰረት አቢይ የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ እንጠይቃለን ፡፡*

*ለህግ የበላይነት መጠበቅ ሁሉም ይረባረብ!!*

*የትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን ኣሜሪካ*
*ዋሽንግተን ዲሲ*